
# ግዮን መፅሔት እንደምርጫዎ ለመድርስ በቅርብ ቀን የማህበራዊ ሚዲያዎችን ትቀላቀላለች

Subscribe

like

share




በአዲስ አደረጃጀትና አቀራረብ

በWebsite:

http://ghion-mag.com

በYouTube:

Ghion Tube ግዮን መጽሔት

በTwiter:

Ghion Magazine

በTelegram:

Ghion Magazine

በFacebook:

Ghion-Mag ግዮን መጽሔት

በInstagram:

Ghion Meg

**መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን !**



የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ ስልክ፡ +251 911 227661 +251 912 165606 +251 118 12 2333
ኢ-ሜይል: enqu2013@ gmail.com ,ghion2011meg@gmail.com

# ግዮን ክፍል ፩


ክፍል አንድ
1-22

ክፍል ሁለት
23-28

ከዐዲሱ መንግሥት ምን ይጠበቃል? 3

የመንግሥት ምሥረታ ብቻውን ለሽብርተኞች ጥፋት መድኃኒት አይኾንም! 4

"እየኾነ ያለውን ሳይ በጣም እደነቃለሁ" 5
አለልኝ መኳንንት ጽጌ (አርቲስት)

ሱዳን እያነጋገረች ወይስ እያደናገረች? 6

ጨዋታ ወፖለቲካ፦ ስለ ሹመት እና "ሺሕ'ሞት!" 7
በሰሎሞን ተሰማ ጂ.



"አሜሪካኖቹ በኢትዮጵያን ሕዝብ ጽናት ተደንቀዋልም ፤ ተሸብረዋልም" 9
ፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማርያም (አል-ማርያም)

ሰላምን መለካት ምን ማለት ነው? 14
በእየሩሳሌም (ሣራ) ሐረገወይን

የህወሓታውያን ሳልሳዊ ሕንፍሽፍሽ 17

ዜና 2

አንደበት 16

ፖለቲካውን ሳናክም ኢኮኖሚው ጤነኛ ሊኾን አይችልም! 19
መታሰቢያ መልዓክሕይወት

ትንታገ ኮሎኔል እስጢፋኖስ ገብረመስቀል 20

ታንክ ተጋፋጩ ሻምበል በቀለ በሬዳ 20

ከሕገ መንግሥት ማሻሻያ እስከ ተደራጀ ዘርፊያ! 21
[ተጠባቂ የብልጽግና መንግሥት አጀንዳዎች]
ይትባረክ ዋለልኝ





ቁጥር 153

ግዮን
ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ መስከረም 29/2014 ዓ.ም
ይጠብቁን

# “አሜሪካኖቹ በኢትዮጵያን ሕዝብ ጽናት ተደንቀዋልም ፤ ተሸብረዋልም”

## “መንግሥት ከወያኔ ጋር ቁጭ ብሎ እንደማይነጋገር የተገነዘቡ ይመስለኛል”

## “አሜሪካ ውስጧ ተቦርቡሮ ያለቀች ሀገር ሆናለች”

ፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማርያም (አል-ማርያም)

*ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም ኑሯቸውን በሃገረ-አሜሪካ ያደረጉ የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ናቸው፡፡ በህወሓት/ኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን ይደርስ የነበረውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ ያለመታከት ለዐሥራ ሦስት ዓመታት “Al Mariam’s Commentaries” በተሰኘው የግል ድረ ገጻቸው በተከታታይ ጦማሮች ለዓለማ አቀፉ ማኅበረሰብ በማጋለጥ ይታወቃሉ፡፡ ከ2010ሩ ለውጥ በኋላም በጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ የአማካሪዎች ካውንስል ዋና ሊቀመንበር ኾነው ተሹመዋል፡፡ ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያምን አሁን ላይ የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እየወሰዳቸው ስላሉ ማዕቀቦች፣ ስለኢትዮጵያ አጠቃላይ ፖለቲካዊና ነባራዊ ጉዳዮች የሚከተለውን ሰፊ ቆይታ ከጋዜጠኛ ፍቃዱ ማኀተመወርቅ ጋር ከሚኖሩበት አሜሪካ አድርገዋል፡፡ መልካም ንባብ!*



**ግዮን፡- የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ላይ የጣለውን ማዕቀብ እንዴት ያዩታል? ጉዳቱስ ምንድነው?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ማዕቀቡ የተጣለው በፈረንጆች ግንቦት 35 ቀን 2021 ነው፡፡ የቅጣቱ ዓይነትም “ቪዛ ሪስትሪክሽን” የሚባለው ነው፡፡ የተወሰኑ ሥማቸው ያልተጠቀሱ ሰዎች በቱሪዝምና በሌላ ጉዳይ ወደ ሀገሪቱ እንዳይገቡ ለማድረግ የወጣ ዕቀባ ነው፡፡ የሚታገዱበት ምክንያት “የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀል መፈፀም፣ ንብረት ማጥፋት እና ወታደሩን መቆጣጠር ባለመቻላችሁ በደል ሰርታችኋልና ወደ ሀገራችን አትገቡም” የሚል ነው፡፡ ወንጀል የፈፀሙትን የመከላከያ አባላት ተጠያቂ ማድረግ ነበረባችሁም የሚል ነው፡፡ እግዱ የተጣለባቸው አካላት ማንነትንም ጠቅሰዋል፡፡ ይኸውም የአማራ ክልል አመራሮችና የልዩ ኃይል አባላት፣ የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት እና በወያኔ በኩል ያሉ ከፍተኛ አመራሮችንም ጭምር ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ቪዛ የሚከለከለው የእነዚህ ሰዎች ቤተሰቦች ካሉ እነርሱ ላይም እገዳው ይሠራል፡፡ በተለይ እንደ ልጅ፣ ሚስት፣ አባትና የመሳሰሉትን ላይ ይጠብቃል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ “የምዕራብ ሀገሮችንም እናስተባብራለን” የሚል ሀሳብ ነው ያለው፡፡ እዚህ ላይ በመጀመሪያው የተጠቀሰው ሕግ “ከአሁን በፊት ሰፋ ያለ የኢኮኖሚና ሴኩሪቲ እርዳታ አቁመናል” የሚል ነው፡፡ ከለከልን የሚሉት እርዳታ በትራንፕ ጊዜ ያስቀሩትን 260 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ በዓመት የሚሰጥ ድጎማ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ከዚህ ገንዘብ ላይ ከ80 እስከ 90% የሚኾነው ከአሜሪካ አይወጣም፡፡ እቃ ሲገዛና ሌሎች ነገሮች ሲከናወኑ የሚያልቅ ገንዘብ ነው፡፡ አብሮ መታወቅ ያለበት ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው ጥሬ ብር እንዳልሆነም ነው፡፡ ስለዚህ እርዳታ ይባላል እንጂ የሚረዱት የራሳቸውን ሰው ነበር፡፡ ለምሳሌ ምግብ ወይም መድሐኒት ከተፈለገ አሜሪካ ያለው አምራች ይሰጣል እንጂ ኢትዮጵያ ገንዘቡ ተሰጥቷት ዓለም ገበያ ላይ ካለው የተሻለውን አይታ የምትገዛው አይደለም፡፡

ይሄ ደግሞ በስፋት የራሳቸውን ገበሬና ነጋዴ ነው የሚያሳድገው፡፡ ከማዕቀቡ ጋር በተያያዘ የሚናገሩት ሌላም ነገር አለ፡፡ ይኸውም “ለምግብ፣ ለትምህርት፣ ሴቶችን ለመደገፍ

የሚደረገውን ዕርዳታ ማዕቀቡ አይነካም” ይላሉ፡፡ እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ይሄን የሚያደርጉት አንድ ሕግ ላይ ተመስርተው እንደኾነ ነው፡፡ አንድ ሚግሬሽን እና ናሽናላይዜሽን የሚባል አጥኚ ቡድን አለ፡፡ ቁጥሩ 212 A3C ይባላል፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ለማንኛውም የውጪ ሰው ቪዛ መከልከል እንደሚችል ይገልጻል፡፡ ስለዚህ አሜሪካ ላይ አላስፈላጊ የኾነ ችግር ይፈጥራሉ የተባሉ ሰዎች በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት ቪዛ ሊከለከሉ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ሌላው በዚህ ማዕቀብ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ሰዎቹ በግል ማን እንዳኾኑ አለመጠቀሳቸው ነው፡፡ በእርግጥ ሥማቸውን ለመጥቀስ ደግሞ አሜሪካዎቹ “ፕራይቪሲ” የሚባል ሌላ ሕግ ስላላቸው ሥማቸውን መጥቀስ አልቻሉም፡፡ ነገር ግን ካስፈለገ የእነዚህ ሰዎች ሥም እንዲጠቀስ የሚፈቅድ ሌላ ሕግ አለ፡፡ ለምን ያንን እንዳልመረጡ በራሱ ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በዓለም ቢታወቁ ሀገር ውስጥ ያለውም ኾነ ሌላው ሀገር በግልፅ ሊያውቃቸውና ተጠያቂ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም “ወንጀለኛ” ናቸውና፡፡ ነገር ግን በቂ ማስረጃ ስለሌላቸው ማንነታቸውን መግለጽ የሕግ ችግር ሊያመጣባቸው እንደሚችል ተገንዝበዋል፡፡ በእንዲህ ዐይነት ምክንያት ሥሙ የጠፋበት ግለሰብ የአሜሪካን መንግሥት በሥም አጥፊነት መክሰስ ይችላል፡፡ ይሄንም ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው የአሜሪካ መንግሥት ማንነታቸውን በዝርዝር ያላስቀመጠው፡፡ ነገር ግን እነዚያ እግድ የተጣለባቸው አካላት አንድ ቀን መግባት እንደማይችሉ ይነገራቸዋል፡፡ ቁጥራቸው ዐሥር ይኹኑ ሃያ ሊታወቅ የሚችለውም አሜሪካ ሄደው ሲጠይቁ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ በዓለም ላይ ቪዛ አገድን ይላሉ ማንነቱን ግን አይገልጹም፡፡ እግድ የተጣለባቸው ሰዎችም ሄደው ቢከለከሉ ምክንያቱ ላይነገራቸው ይችላል፡፡ ለምን እንደተከለከሉ ቢጠየቁም ተጠያቂው አካል የማብራራት ግዴታ የለበትም፡፡

**ግዮን፡- ማዕቀቡ በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትለው ቀጥተኛ ጉዳት ምንድነው?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ጉዳቱን ለመናገር ተጎጂዎቹ እናማን እንደኾኑ አልታወቀም፡፡ ያልታወቁ ሰዎች አሜሪካ የመግባት መብታቸው ይገፈፋል የሚል ብቻ ነው የተገለጸው፡፡ ሌላው ጉዳት አሜሪካ ይኼን መሠል ማዕቀብ ጣለች እየተባለ ለፕሮፖጋንዳ መዋሉ ነው፡፡ ሥም ለማጥፋትና የፖለቲካ ጥላሸት ለመቀባት ነው የሚጠቀሙበት፡፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካን ከአፍጋኒስታን አወጣጥ ያየ ሁሉ ምንም ቢሉ ግድ የማይሰጡበት ደረጃ ደርሰዋል፡፡ እ.ኤ.ኤ መስከረም 17 ባይደን ወደፊረመው ጉዳይ ስንመጣ ሦስት ሕጎች ላይ የተመሠረተና ትንሽ ለየት ያለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ከፍ ሲል የጠቀስኩት የሚግሬሽን ሕግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ “National Emergency Academy” የሚባል አለ፡፡ ለፕሬዝዳንቱ ልዩ ሥልጣን የሚሠጥ ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ “Internatinal Emergency Economic Act” የሚባል አለ፡፡

እነዚህ ሦስቱን መሠረት አድርጎ ነው ፕሬዝዳቱ ይሄን ማዕቀብ ያወጣው፡፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው የተለያየ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ ሦስቱ ሕጎች ላይ የተመሠረተ 14046 የሚል ማንኛውም ሰው በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ በራሱም ኾነ በሌላው ይኼን ነገር በማድረግ የአሜሪካ መንግሥት ከጠረጠረውና “ሰላምን ሊያቃውስ ይችላል” ብሎ ካመነ እና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይፈፅማሉ የሚል ምልከታ ካለው እርዳታ እንዳይደርስ እንቅፋት ሆነዋል ብሎ የለያቸው ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ ሊያቀርቡ የሚችሉት ማስረጃ የለም፡፡

የአሜሪካ መንግሥት ይኼን የሚያደርገው በትሬዠሪ ዲፓርትመንቱ በኩል ነው፡፡ ምክንያቱም ትሬዠሪ ዲፓርትመንት ማለት ገንዘብ ቤት ማለት ነው፡፡ የሚሠራው ሥራ ከዚያ ጋር ስለሚገናኝ ነው፡፡ ለምሳሌ የግለሰቦቹ ማንነት ታውቆ ቢኾን አሜሪካን ሀገር ንብረት ካላቸው በአሜሪካ መንግሥት እጅ ይወድቃል፡፡ ለምሳሌ የነዳጅ ማደያ ካላቸው በአሜሪካ መንግሥት እጅ ሥር ይኾናል፡፡ የባንክ አካውንት ላይ 1 ሚዮዮን ብር ቢኖረው ያንን ብር ማግኘት አይችልም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚታየው ደግሞ ይኽ ሕግ የፀናበት ሰው ብድር መውሰድም እንደማይችል ነው፡፡ ቤት አትርፎ መሸጥ አይችልም ፤ ንግድ ፈቃድ ማውጣት አይችልም፡፡ በሌላ በኩል የታገደውን ግለሰብ መርዳት የፈለገ ማንኛውም አካል በሕጉ መሠረት ተጠያቂ ይኾናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ መረዳዳት አይቻልም፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው እነዚህ ነገሮች የሕጉ መስፈርት ሲኾኑ እንዴት ነው ሥራ ላይ የሚውሉት የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይኽ ጥያቄ አሁን ባለው ሁኔታ አልተመለሠም፡፡ ሥራ ላይ የሚውለው ስቴት ዲፓርትመንትና ትሬዠሪ ዲፓርትመንት እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተስማምተው መርሃ ግብር ያወጣሉ፡፡

በዚህም መሠረት ማንነታቸው ተለይቶ በየቦታው ትዕዛዙ ይላካል፡፡ ከዚህ አካያ ይኼ ማዕቀብ ተግባራዊ እንዲኾን ገና ድንጋጌው አልወጣም፡፡ ማዘዣው ወጣ እንጂ እንዴት ኾኖ በሥራ ላይ እንደሚውል እየተጠበቀ ነው፡፡ እዚህ ላይ ልገልፅ የምሻው ነገር ስቴት ዲፓርትመንት “ጊዜ እንሰጣቸዋለን” ያለውን ሃሳብ ነው፡፡ ማዕቀቡን ተግባራዊ ለማድረግ ከሣምንት እስከ ወር የሚቆይ ጊዜ ሰጥተዋል፡፡ ይህ በመኾኑ የሚመጣው ጉዳት ምንድነው የሚለው አንደኛው ጥያቄ ነው፡፡ ይኼ በብዙ መንገድ ሊታይ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ይኽ ነገር መሥፈርቱ በስቴት ዲፓርትመንትና በትሬዠር ዲፓርትመንት እስኪወጣ ድረስ አይታወቅም፡፡ የትዕዛዙን አቋም እንጂ አሠራሩን አናውቀውም፡፡ ከዚያ ውጭ ደግሞ ለምሳሌ አንተ የተጠቀስከው ሰው ብትኾንና እኔ ዜጋ ብኾን ከአንተ ጋር ያለኝን የንግድ አጋርነት እንዴት ይነካዋል የሚለው ጥያቄም መሠረታዊ ነው፡፡ የፍርድ ችግር የሚያጋጥመውም በዚህ ሰዓት ነው፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ ይሄ ነገር የሚመለከታቸው ምን ዐይነት ሰዎች ናቸው የሚለው ነው፡፡ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ከተጠረጠሩት ሰዎች መካከል ምን ያህሉ አሜሪካ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ? የጦር መኮንንኖቹስ ምን ያህል ናቸው? ከአማራ ክልል አመራሮች እነማንን ይነካል የሚለው ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ ያን ያህል ንብረት ኖሯቸው እዚያ ሀገር ከቆዩ በእኔ አስተያየት ዜግነት ወስደዋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ዜግነት ሳይወስዱ የዚያን ያህል ሀብት ኢንቨስት ያድርጋሉ ብዬ አላምንም፡፡ ዜግነት ከወሰዱ ደግሞ እግዱ አይመለከታቸውም፡፡ ስለዚህ “ውሾቸም ይጮሃሉ ግመሎቹም ይኼዳሉ” የሚሉት ዐይነት ተረት ነው የሚኾነው፡፡ በሌላ በኩል ከዚህ ሌላ ሊያመጡ የሚችሉት ምን ሃሳብ አለ የሚለውም ጉዳይ መቃኘት አለበት፡፡ እነርሱም ይሄን ጉዳይ ጠቋቁመውታል፡፡ ከዚህ አልፈውም የኢኮኖሚ ጉዳይ ሊያደርጉት እንደሚችሉ ጠቅሰዋል፡፡ ሊኾን ይችላል፡፡ በዓለም ላይ ኾነን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እንጎዳለን ወደሚለው መንገድ ከሄዱ የኢኮኖሚ ጦርነት ከፍተዋል ማለት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያና የአሜሪካ ጉዳይ የኢራንና የአሜሪካ ዐይነት ይኾናል ማለት ነው፡፡ እዚያ ድረስ ደፍረው ከሄዱ ግንኙነት አይኖርም ማለት ነው፡፡ በዚያ ልክ ማድረግ ከፈለጉ ኢትዮጵያን በኢኮኖሚ ማሽመድመድ ፈልገዋል ማለት ነው፡፡ ይኼን ካደረጉ ለአፍሪካም ጠንቅ ይዞባቸው ሊመጣ ይችላል፡፡ ኢምፔሪያሊዝም መኾኑ ስለሚታይ ለኢትዮጵያ የተለየ ገፅታ ይሠጣታል፡፡

ከአሜሪካ ጋር ትልቅ ትግል ተፈጥሯል በሚል ሌላው አፍሪካ ከጎኗ ኾኖ ኢትዮጵያ በታሪኳ እንዳሳየችው ለዓለም ተምሳሌት ትኾናለች ማለት ነው፡፡ ጥያቄው ግን አሜሪካ ይህ እንዲሆን ትፈልጋለች ወይ ነው፡፡ እንዳየናቸው ሃያ ዓመት አፍጋኒስታን ቁጭ ብለው ያመጡት ውጤት የለም ፤ ተሸንፈው ነው የወጡት፡፡ ኢትዮጵያን በዚህ መልኩ እናጠቃለን ቢሉ ምን ዓይነት ውጤት እንደሚጠብቃቸው አዲስ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ቬንዙዌላን ሞክሩ፣ ኢኮኖሚያዊን አበላሹ፣ የቻሉትን ሁሉ ሞክሩ ግን አልኾነላቸውም፡፡ ይኼ አካሄዳቸው ጥላቻ ያተርፍላቸው ይኾናል እንጅ የትም ሀገር ሊሳካላቸው አይችልም፡፡ በተለይ ኢትዮጵያን በተመከተ አጥፍተን እንጥፋ ካሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የባሰ የመንፈስ ጥንካሬ ይሰጡታል፡፡ ቢራብም ቢጠማም ይህችን ቀን እናልፋለን እያለ ከአሜሪካ ጋ ፍልሚያውን ይቀጥላል፡፡ በእኔ አተያይ የበለጠ የሞራል ጥንካሬ ይሰጣል፡፡ የሕዝቡን አንድነት ያመጣል፡፡ እናም ወደዚያ ይኼዳሉ ብዬ አላስብም፡፡

ሌላ እዚህ ጋር የምጠቅሰው ነገር የኢትዮጵያን ሕዝብ ጽኑነት ማየታቸውን ነው፡፡ በጣም ተደንቀዋልም ፤ ተሸብረዋልም፡፡ ምክንያቱም ወያኔ እንደነገራቸውና እነርሱም በታሪክ እንዳዩት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲናቆርና በዘር ሲለያይ ነው የሚያውቁት፡፡ በታሪካችን የውጭ ጠላት ሲመጣ አንድ እደምንኾን ቢያውቁም እንደተረት ነበር የሚቆጥሩት፡፡ የዓድዋን ድል እነርሱ እንደ ተረት ነው የሚያዩት፡፡ አሁን ግን በተግባር ዳግም አይተውት በጣም የደነገጡ ነው የሚመስለኝ፡፡ ምክንያቱም በእነርሱ ስሌት ኢትዮጵያ ትበታተናለች ብለው ነው ምርጫ አይደረግ ያሉት፡፡ ምርጫው ተካሄዶ ግን አንድ ጥይት አልተተኮሰም፡፡ የእነርሱ ምርጫ ከሕዳር ጀምሮ እስከአሁን እየተቆጠረ ነው፡፡ እኛ ግን አንድ ጥይት ሳይተኮስ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የተቀበለው ምርጫ አካሂደናል፡፡ ለዚያ እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን አላሉንም፡፡ ስለዚህ ይህ እሳቤያቸው አልሠራም፡፡

ወያኔ በሁለት ሳምንት ሁሉን ነገር ጨርሰን እንሰጣችኋለን አላቸው፤ እርሱም አልሠራም፡፡ የተናጠል ተኩስ አቁም ተብሎ ነበር እርሱም እንዳሰቡት ሳይኾን ቀረ፡፡ ስለዚህ እቅዳቸው በሙሉ ፈርሷል፡፡ አሁን በሥልጣን ላያ ያሉት እነብሊንከንና የመሳሰሉት ምንም የማያውቁ ሕጻናት ናቸው፡፡ ስቴት ዲፓርትመንት በትራንፕ ጊዜ ብትንትኑ ወጥቷል፡፡ ለምሳሌ ብሊንከን ኮንግረስ ሄዶ ሲናገር ስቴት ዲፓርትመንት ባዶ ነው፡፡ ድሮ የነበሩት ተባረዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ዐይነቱን ውሳኔ ለመወሰን አቅሙ የላቸውም፡፡ በመኾኑም እነርሱ በሚመስላቸው ብቻ ይናገራሉ ፤ ሊያዙን ይሞክራሉ፡፡ ይኽን የሚያደርጉት ደግሞ እንደድሮው እየመሰላቸው ነው፡፡ ድሮ አሜሪካ ስታዝ ይሠራ ነበር፡፡

አሁን ግን አሜሪካ ቀፎ መኾኗን ትራንፕ



አሳይቶናል። ምርጫ ማካሄድ እንኳን አቅቷቸው እስካሁን እየተገዙ ነው ያሉት። ሃያ ዓመት የቆዩበት ሀገር ላይ ነው ሰው ከአውሮፕላን እየተወረወረ የወደቀበት። ማን እነርሱን ይህን ያህል ይፈራቸዋል የሚል አስተያየት ነው ያለው። ሌላው ደግሞ እነርሱ ያሰቡት ዳያስፖራውን እንደድሮው ተጠቅመው እዚያው አገር ተቃውሞ መፍጠር ነበር፤ ይኼም አልሠራላቸውም። እንደውም ዞሮ ለእነርሱ እንቅፋት ኾነባቸው። ለምሳሌ እኔ በእነርሱ ሕግ የሰለጠንኩ ነኝ። በማንኛውም ደረጃ ከእኔ የበለጠ ለእነርሱ የሚቀርብ ሰው አልነበረም። ነገር ግን ይኼ ነገር ሲመጣ ባሰለጠኑኝ መንገድ ወደ እነርሱ ዞርኩባቸው።

**ግዮን፡- አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ እንዲህ ዐይነት አቋም የያዘችው ለምንድ ነው? የኢትዮጵያስ ምላሽ ምን መኾን አለበት?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- አሜሪካ ኢትዮጵያን ለምን ጠላች ስንል የአሜሪካ ሕዝብንም የሚጨምር ይመስለኛል። በመጀመሪያ የባይደን አስተዳደር እና የሱዛን ራይስ አካሄድ በአንድ ፈርጅ የሚታይ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የአሜሪካ ሕዝብ ነጭ ይኹን ጥቁር ስለአፍሪካ ግድ የለውም። ኮቪድ 19 ያመጣበትን መዓት እየታገለ ያለ ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያ ብትነድ ጉዳያቸው አይደለም። እራሳቸውም በነፍስ ውጭ ግቢ ውስጥ ናቸው። አሁን ይኼን የሚያራምዱት ኦባማ በነበረበት ጊዜ ወያኔን ሲደግፉ የነበሩት እነ ሱዛን ራይስ እና እነ ብሊንከን በባይደን መንግሥት ውስጥ ገብተው ነው። በተለይ በኢትዮጵያ ፖሊሲ ላይ ተጠያቂዋ ሱዛን ራይስ ናት። ይሄን በተመለከተ ማስረጃውን አስቀምጫለሁ። ወያኔ ጥቅምት ሃያ አራት በጀመረው ጥቃት መደምሰሱን ስታውቅ አድኑልኝ እያለች ስትማፀን ነው የነበረው።

ስለዚህ የአሜሪካ ጥላቻ የተፈጠረው በሱዛን ራይስ በኩል ነው። ለዚህ ደግሞ ተጠያቂ ነች። ምክንያቱም ሱዛን ራይስ ታስታውስ ከኾነ መለስ የሞተ ጊዜ መጥታ የተናገረችው ነገር ነበር። የመለስን ሌጋሲ እንደምታስቀጥልም በይፋ ተናግራለች። አሜሪካ ያለቻችሁን እስከሠራችሁ ድረስም እንደግፋችኋለን ብላም በገሀድ ተናግራለች። ስለዚህ እርሷ ናት አሁን እየዘወረች ያለችው። በሁለተኛ ደረጃ አሁን ኢትዮጵያ ላይ እየሠራች ያለችው ኤርትራ ላይ እ.ኤ.አ 2009 ላይ ሠርታው የነበረውን ነው። ከ1998 እስከ 2000 በነበረው ጦርነት የመለስ ተላላኪ ነበረች። ኢሳይያስን ሄዳ ይኼን አድርግ ያን አድርግ ስትለው ዞር በይ ብሎ በካልቾ ጠልዞ አባረራት። ያኔ ዞር አለችና የተባበሩት መንግሥታት ሄዳ አልሸባብን ይደግፋል በማለት ማዕቀብ አስጣለች። የሀገሪቱን ኢኮኖሚም አሽመደመደች። አሁንም ያንን አካሄድ ነው እየተከተለች ያለችው። ስምንት ጊዜ የተመድ ጸጥታው ም/ቤት በኢትዮጵያ ላይ እንዲሰበሰብ ሞክራለች። አንዴ በቱንዝያ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሌሎች በኩል ጥራለች፤ ግን አልሠራላትም።

አሁን የቀረው አሜሪካ ምን ማድረግ ትችላለች የሚለው ነው። እርሷም ወደዚያው ነው የተመለሰችው። ሦስተኛው ነገር ሎቢን በመጠቀም በምክር ቤቱ ላይ ተጽዕኖ አድርጋ ከምክር ቤቱ እንደ ድንጋጌ ለማሳለፍ መሞከርን ነው። ይኼ ደግሞ በሰብዓዊ መብት ሰዎች ይናፈሳል። ነገር ግን ዓለም ላይ በአሁኑ ግዜ ትግራይ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ የፈለገ ነገር ቢኾን ማንም ሰው ጉዳዩ አይደለም። ከአሁን በፊት የነበራቸው አሠራር አሜሪካን ሀገር ሄደው በሚዲያ ለፍፈው ነጩን ማነሳሳት ነበር። ይሄ 1994 ላይ “we are the world” ተብሎ ተነግዶበታል። ዛሬ ጥቁሩም የሕልውና ፈተና አለበት። የሚበላውና የሚጠጣው የለውም። ስለዚህ ነጩን ለማነሳሳት ነበር የሚሠሩት።

በነገራችን ላይ አሜሪካን ሀገር ያለውን የኑሮ ችግር ይኼ ነው ብሎ መግለፅ በጣም ይከብዳል። በተለይ ከታች ላሉት ከባድ ነው። ለምሳሌ 12 ሚሊዮን ሰዎች ኪራያቸውን ሳይከፍሉ ዓመት አልፏቸዋል። ይሄን ጎግል ላይ ማየት ይቻላል። ሀገሪቷ ውስጧ ተቦርቡሮ አልቋል። በነጩና በጥቁሩ መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ልዩነት ወይም የሀገሪቱን ቀፎነት ዶክሜንት አድርጌዋለሁ። ከአሁን በፊት ይህን ስናገር ሰው ይስቅ ነበር። አሜሪካ የምናውቃት አይደለችም አሁን ባዶዋን ቀርታለች። ሁሉም ተከፋፍሏል። አፍሪካ አሜሪካ አለ፤ ነጭ አለ፤ ኢስትና ዌስት አለ፣ ሬድ እና ብሉ ሴት የሚባል አለ። ይኼ ምርጫውም ላይ በደንብ ታይቷል። ግማሹ “ዓለም ለምን አይጠፋም እንፈልግም አታነካኩን” የሚል ነው። የእነ ኦባማ ሰዎች ደግሞ በዓለም ላይ ያለ ምሥራቆችን ሰብስበንና እንደ አዲስ ፈጥረን እኛ በምንሰጠው ትዕዛዝ እናስተዳድራለን የሚሉ ናቸው። ይኼ ደግሞ በትራንፕ ተከታዮች በኩል ተቀባይነት የለውም። ስለዚህ በየቦታው ያሉ ትንንሽ ኤሊቶች በሎቢስቶች እየተነዱ ነው። ይኼን ነገር የሚያራግቡት ከውጭ ደግሞ የምዕራባውያን ሚዲያዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካኖች ጥላቻና ንቃቱ የመጣው ዐቢይ አሕመድ የተባለ ወጣት ከየት ቢመጣ ነው ያልነውን የማይሰማን ከሚል ብሽቀት የተነሳ ነው። “ኢትዮጵያን ምንድን ናቸው? ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ እኮ አንድ ሕዳጣን ሲገዛቸው የነበሩ ናቸው። እኛን እንዴት?” የሚል አስተሳሰብ አላቸው። ሕዝቡንም በጣም ንቀውታል። መተባበር አይችልም፤ አንዱ ሌላውን ማጥፋት ይፈልጋል የሚለው ነገር በጭንቅላታቸው በደንብ ሰርጎ አምነውበታል። ወያኔም የሚነግራቸው ይኼን ነበር። ስዚህ ከጥላቻም በላይ ንቀት ያለባቸው ይመስለኛል።

“እድሜ ልካቸውን በረሃብ የኖሩ” ብለው ነው የሚንቁን። “አንድ ቀን ራሳቸውን መግበው የሚያውቁ እንዴት እኛን ይጋፉናል” የሚል እብሪት አለባቸው። በአፍሪካ ፕሬስ የትራንፕ ረዳት ሴክሬተሪ የነበረው ታቦር ናዥ እኮ ይሄን ግልፅ አድርጎ ተናግሯል። ኢትዮጵያውያንን ግን አያውቋቸውም። የአሜሪካ ትዕዛዝ በወጣበት ቀን በሰዓታት ልዩነት ነበር የኢትዮጵያ መንግሥት ምላሽ የሰጠው። ስለዚህ ይኼ መልስ ራሱ ሳያስደነግጣቸው አይቀርም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደብዳቤውን በግልጽ የጻፉት ዓለም ጉዳዩን እንዲመለከተው ነው። “የፈለጋችሁትን አድርጉ ግን ቁርጥ ያለመልስ እንሰጣችኋለን” የሚል ነው።

እንግዲህ በደብዳቤው እንዳየነው በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ክብርና አንድነት ድርድር የለምና አታስቡት ተብለዋል። በሁለተኛ ደረጃ እዛ ቁጭ ብላችሁ ኢትዮጵያን እንመራለን የሚለውን ሃሳባችሁን ብትተውት መልካም ነው የሚልም ነው። በሦስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው “ገንዘብ አንሰጥም የምትሉትን ነገር ከፈለጋችሁ አስቀምጡት አንፈልገውም። ብቻ በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ገብታችሁ አትፈትፍቱ” የሚል ነው። “ነገር ግን ገብተን ኢትዮጵያ ላይ ጥፋት እናደርሳለን ካላችሁ ለመከላከል ዝግጁ ነን፤ ታሪካችንም የሚያሳየው ያንን ነው።” የሚል ነው። ከዚህ አልፎ አመጣጣቸው ወዲ አዲስ ቅኝ ግዛት ስለኾነ አፍሪካን አስተባበረን በፓን አፍሪካኒዝም ደረጃ እንዋጋችኋለን የሚልም ነው። ስለዚህ ደብዳቤው ቁልጭ አድርጎ ነው የነገራቸው። ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሰሞኑን በጉባኤው ያረጋገጡላቸው ይኼንኑ ነው። እነርሱም በምንም ዐይነት መንገድ የኢትዮጵያ መንግሥት ከወያኔ ጋር ቁጭ ብሎ እንደማያወራ የተገነዘቡ ይመስለኛል። የኢትዮጵያ መንግሥት ቢፈቅድላቸው እንኳ ሕዝቡ አይፈቅድም። ስለዚህ ያከተመለት ነገር ነው። እነርሱ ደግሞ በሕጋቸው ቁጭ ብለው መነጋገር ካልቻሉ ማዕቀቡን እንደሚጥሉ ገልፀዋል።

**ግዮን፡- እርሶና እርሶን መሰሎች በኢትዮጵያ ላይ ሊደረግ የታሰበውን ጫና ለመቀልበስ ምን ሚና ይኖራችኋል? ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙ ተቋማት እንቅስቃሴስ ምን ይመስላል?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ ከ2005 መጨረሻ ጀምሮ እስካሁን በየሳምንቱ የእነርሱን ምሥጢር አጋልጫለሁ። ይኼ መደበኛ ሥራዬ ነው።

፡ ሕዝቡን በማስተማር የሚሠራውን ተንኮል ምን እንደኾነ አሳይቻለሁ፡፡ ወያኔዎች ይስፋፋሉ ብዬ እንደጠቆምኩት ወዲያው ተስፋፍተዋል፡ ፡ የዘር ጭፍጨፋ ያደርጋሉ ብዬ በጠቆምኩት መሠረትም በሁለት ሳምንት ውስጥ ተግብረውታል፡፡ ብቻ የምናገረቸው ነገሮች ተግባራዊ የሚኾኑ ናቸው፡፡ እኔ ይኼን ነገር ያወጣሁት ገና የባይደን አስተዳደር ሲጀምር ጥር ላይ ነበር፡፡ የመጀመሪያው እቅዳቸው ወያኔን መመለስ እንደኾነ፣ ቻይናን ኢትዮጵያ ውስጥ ደግ አመድ ማድረግ፣ ምርጫውን ማበላሸት ወዘተ ብዬ ዘርዝሬ አስቀምጬ ነበር፡፡ ስለዚህ የእኔ ሚና ያለኝን እውቀትና ልምድ ተጠቅሜ እነሱን ግልፅ በኾነ መንገድ ማጋለጥ ነበር፡፡ አንድ ነገር ሲያደርጉ እኔ ምሥጢሩን ይገፔ እወጣለሁ፡፡ ማዕቀቡን አስመልክቶም በሁለት ሳምንት ቀድሜ ተናግሬ ነበር፡፡ በሌላ በኩል የእነርሱን ፖሊሲ በመገምገም ለእነርሱም ለኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲረዳ ማድረግ ነው፡፡ እነርሱ ራሳቸው ሕጋቸውን አጥርተው አያውቁትም፡፡ ስለዚህ አንድ ነገር ሲያደርጉ ሕግ ጥሰው እንደሚሰሩ እጠቁማለሁ፡፡

ይኼ ደግሞ ትንሽ የሞራል ኪሳራ ሳይጥልባቸው አልቀረም፡፡ ሌላው በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል የሚደረግ ትግል ሲኾን እኔ ሰፋ ባለ መንገድ እጠቀምበታለሁ፡፡ በተለይ ቲውተር ላይ የሚቀመጥ ጽሑፍ ይነበባል፡፡ መልስ መሥጠት ባይቻልም የተፈላገውን ሃሳብ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ አንድ ሳምንት ሳላሳልፍ 16 ዓመት ነው የተሟገትኩት፡፡ ሌላው እውነት መናገር ነው፡፡ ሁልጊዜ እውነት እናወጣባቸዋለን፡ ፡ ለጊዜው ሊያወናብዱን ቢሞክሩም እያሳደድን በእውነት ሴራቸውን እናከሽፍባቸዋለን፡፡ እዚህ ላይ መጥቀስ የምፈልገው ሌሎች እንደኔ ያሉ ሰዎች የት ናቸው? ዙም ላይ ቁጭ ብሎ መፈላሰፍ ሳይኾን እነዚህ የኢትዮጵያ ተፃራሪ ኃይሎች በግለሰብም ይሁን በተቋም ደረጃ መሟገት እንዴት ተሳናቸው?! የኢትዮጵያ ምሁራን በአሁኑ ጊዜ ጠመንጃ ይዘን መሯሯጥ አንችልም፡፡ ሰለዚህ ጠመንጃችን ብዕር መኾን አለበት፡፡ ጠላትም እየመጣብን ያለው በዚያ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ CNN አንድ ነገር ሲያደርግ በጠመንጃ አይደለም፡፡

*ግዮን፡- በአሜሪካ የእርሶን ጽሑፍ እያዩ ትክክል አለመኾናቸውን የሚነግርዎት ትልልቅ አሜሪካውያን አጋጥሞት አያውቅም?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- የእኔ ጽሑፍ በጣም ኃይለኛ ስለኾነ እኔን ኮት ማድረግ እንኳን ሰው ይፈራል፡፡ እኔ ስጽፍ ማሥረጃውን አስቀምጬ ነው፡፡ ጽሑፌ ምሕረትና ማባባል የለውም፡፡ ለምሳሌ አልጀዚራ የዛሬ ስድስት ወር ገደማ ኢንተርቪ እንድርግህ ብለው ሁለት ሳምንት ከጎተጎቱኝ በኋላ ዘግተውኝ ሊያልፉ ሞከሩ፡፡ እኔ ግን ከእነርሱ ጋር በኢሜል የተነጋገርነውና ሌሎቹንም በሙሉ አስቀምጬ ነበር፡፡ ያንን አተምኩት፡፡ ለምን ሃሳባቸውን እንደቀየሩ መልስ መሥጠት አልቻሉም፡፡ ብዙ አንባቢያን እንዳለ አውቃለሁ፡፡ ለእኔ በግል የሚነግሩኝ ሰዎች አሉ፤ ያስቀመጥኩትን ነገር አምኖ ከመቀበል ውጭ መልስ የላቸውም፡፡ እስከ ዛሬ አንድም ሰው 16 ዓመት ስጽፍ ሙሉ መልስ የሰጠኝ የለም፡፡ ከ1200 በላይ ሣምንታዊ ጽሑፎችን አቅርቤያለሁ፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ግን በደንብ እንደሚያነበኝ አውቃለሁ፡፡ አንድ የአሜሪካ ኤምባሲ የሚሰራ ሰው እንደነገረኝ ሰኞ ሰኞ ተቀምጠው የእኔን ጽሑፍ ገምግመውና አትመው ፋይል ያደረጉታል፡፡ ስለዚህ በደንብ እንደሚከታተሉ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ በዚያ ደረጃ ተሠሚነት አለኝ፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ላይም አንዳንዴ ጽሑፎቼን ይገመግማሉ፡፡ ይኼ ራሱ ከሠላሳ ሚሊዮን በላይ የሚያየው ነው፡፡

*ግዮን፡- የጠቅላይ ሚ/ሩን ደብዳቤ እርስዎ እንዴት አዩት?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ እንዲህ ዐይነት ደብዳቤ አልጠበቅኩም፡፡ በታሪክም በልምድም በዲፕሎማሲም እንደምናውቀው አንድ መንግሥት አንድ ነገር ሲናገር ቢያንስ ለሁለት ቀን ጉዳዩ ተብላልቶ ነው መልስ የሚሰጠው፡፡ ነገር ግን በአራት ሰዓታት ውስጥ መልስ ሲሰጥ ምን ዐይነት ታሪካዊ ነገር እንደኾነ መገመት ይቻላል፡፡ ሁለተኛ ነገር እኔ እስከማውቀው ድረስ ሁለት ያገር መሪዎች በግልፅ ደብዳቤ ሲነጋገሩ ሰምቼም ታሪክ ላይ አንብቤም አላውቅም፡፡ ወይ ስልክ ይደዋወላሉ ወይ በዲፕሎማሲ ይግባባሉ እንጂ በዚህ መልኩ ታይቶ አይታወቅም፡፡ ሦስተኛ መልሱ ሕጉን በምን ጊዜ አንብበውት በምን ጊዜ ፃፉት የሚያስብል ነው፡፡ ለዚያ ሀሳብ መልስ እንዴት በአራት ሰዓት ውስጥ ተዘጋጅቶ ደረሰ የሚለው በጣም አስደናቂ ነው፡፡ የሰዓቱ ጉዳይ ታሪካዊ ሲኾን ምላሹም በራሱ ታሪካዊነት ያለው ነው፡፡

ታሪካዊነቱ በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያን አቋም ግልፅ በኾነ መልኩ ማስቀመጡ ነው፡ ፡ ኢትዮጵያ ራሷን አልምታ ወደብልፅግና እንደምትሄድና እነርሱን እንደማትፈልጋቸው ይገልፃል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ወያኔን ተገን አድርጋችሁ መጥታችሁ ሀገራችንን እንበጥብጥ የምትሉት ነገር አይፈቀድም የሚል ነው፡፡ እናንተ እኛን ልታዙን አትችሉም፡፡ ምክንያቱም ሉዓላዊነት እና ታሪክ ያለን ሀገር ነን፡፡ ይኼን ጥሳችሁ ብትመጡ ውርደት ይጠብቃችኋል የሚል ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ አጠቃላይ እቅዳችሁ ይገባናል፡፡ ድሮ ቅኝ ግዛት ያወጣውን አሁን በኒውኮሎኒያልዝም ለመመለስ ነው የምትፈልጉት፣ እርሱ ግን አይሠራም፡፡ ለእርሱም ፓን አፍሪካኒዝም የመሠለ መድኃኒት ፈጥረናል የሚል ነው፡፡ ይኼ አባባል ደግሞ ለእኔ የሚገባኝ መደመርን በሥራ ላይ እናውለዋለን በሚል ነው፡ ፡ አፍሪካዊ ዲያስፖራ የሚደምሩን ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ በታሪክ አንድ ነን፡፡ በጭቆና አንድ ነን፡ ፡ እነዚህን መከራከር የምንችለውስንደምር ብቻ ነው፡፡ ካስፈለገ ፓን አፍሪካኒዝም ሊባል ይችላል፡ ፡ ይሄ መደመር የሚለው አስተያየት በአህጉር ደረጃ ብቻ ሳይኾን በቀጠናውም የሚሠራ ነው፡፡

ምክንያቱም በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ሀገሮች "ኢኮኖሚያችንና መዋቅራችንን አንድ እናደርጋለን፣ ይህ ከኾነ ኢትዮጵያ ኃይል ይኖራታል" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ አኳያ ትልቅ መልዕክት ነው የተላከላቸው፡፡ በጥቀሉ የመጨረሻው መልዕክት አንበገርም የሚል ነው፡፡ ልታንኳቁሉን ትችላላችሁ ነገር ግን አታሸንፉንም የሚል መልዕክት ነው ያለው፡፡

*ግዮን፡- በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት እያንሰራራ ያለውን የፓን አፍሪካኒዝም አካሄድ እርሶ እንዴት ያዩታል? የአፍሪካውያን ሚናስ ምን መኾን አለበት?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- አንደኛ ፓን አፍሪካኒዝም በእነ ዑክሩማ ጊዜ የታሰበ ነው፡፡ አስተሳሰቡም አፍሪካን ወይም በዓለም የተበተነውን ጥቁር አፍሪካዊ ሁሉ ማስተባበር ነው፡፡ እነዚህ አካላት ታሪካቸው ያስተሳስራቸዋል፡፡ ጠላቶቻቸው ማን እንደኾኑ ያውቃሉ፡፡ ከ15ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የበታተናቸው ባርነት ነው፡፡ የነጭ የበላይነት እየፈጠረ ያለውን ነገር ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ብዙ የሚያስተባብሩን ነገሮች በመኖራቸው እኛ አፍሪካውያን ራሳችንን ነፃ አውጥተን በሁሉም ነገር መደራጀት እንችላለን የሚል ነው፡፡ ያንን ካደረግን የሚነካን የለም፡፡ በቅኝ ግዛት ጊዜ ያደረጉት አንዱን ከሌለው መከፋፈል ነበር፡ ፡ አሁን በኒውኪሎኒያዝም ዘመን ማድረግ የሚፈልጉትም ያንኑ ነው፡፡ ይሄው "ትግሬ፣ አማራ፣..." የሚሉትም ለዚያው ነው፡፡ እርሱም እንደማይሰራ ተገንዝበዋል፡፡

እንግዲህ አንተ ፓን አፍሪካኒዝም ያልከው እኔ መደመር ነው የምለው፡፡ ምክንያቱም መደመር የአሠራር መንገድ አለው፡፡ ፓን አፍሪካኒዝም እንደ አይዶሎጂ ነው፡፡ ይመራል እንጂ እንዴት እንደሚሠራ አያመላክትም፡ ፡ መደመር ግን አሠራሩን ጭምር ያብራራል፡ ፡ ለምሳሌ ፓን አፍሪካኒዝም በቲዮሪ ደረጃ ብዙ ታሪክ አለው፡፡ በቀጠናው እንኳን ሲታይ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያና ኤርትራ ከተደመሩ ምን ዐይነት ቀጠናዊ ለውጥ እንደሚያመጡ ያሳያል፡ ፡ ዑጋንዳና ኬነያን ከጨመርን ደግሞ በኢኮኖሚ ደረጃችን በዚያው ልክ እናድጋለን፡፡ ከዚያ አልፎ ወደ አፍሪካ ሀገራት ከቀጠልን ደግሞ የገዘፈ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ የአፍሪካ ቀንድ ናሙና ትኾናለች ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ፓን አፍሪካኒዝም የሚባለውን ነገር መደመር ነው የምለው፡፡ ምክንያቱም ኃሳቡ ተመሳሳይ ነው፡፡ እዚህ ጋር መጠቀስ ያለበት ሌላ ነገር ኢትዮጵያ አሁን ለዓለም እያሳየች ያለችው ነገር ሀገሪቱ ላይ መደመር በትክክል መሥራቱን ነው፡፡ "ወያኔ መጣ" ሲባል የጎሳ ልዩነት ጠፍቶ ሕዝቡ ተደመረ፡፡ ጠላታችን ከተወገደ በኋላ ደግሞ መደመሩ ፊቱን ወደ ኢኮኖሚው ያዞራል፡፡ አሁን በዘማቹ ወጣት በኩል አብሮ መቁሰል፣ አብሮ መራብ፣ አብሮ መጠጣት ተለምዷል፡፡ ስለዚህ ከድል በኋላ "ወያኔ ጠፍቷል፣ አሁን ያለው ጠላት ድህነት ነው" ተብሎ ይነገረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ዳግም መደመር በሥራ ላይ ይውላል ማለት ነው፡፡

*ግዮን፡- ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያለን ግንኙነት እንዴት ይቃኛል፡፡ በተለይ ሱዳንና ኬንያ ከብሔራዊ ደህንነታችን አንጻር ያሉበት ቁመና እንዴት ይገመገማል?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- ሱዳን ሕልውና ሥጋት ውስጥ የገባች ሀገር ናት፡፡ ለምሳሌ አሁን በፖርት ሱዳን በኩል ያለው ግዛቷ ተዘግቷል፡ ፡ ዳርፉር ራሷን ችላለች ማለት ይቻላል፡፡ በአመራሩ መካከል ትልቅ ልዩነትና መከፋፈል አለ፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ እንዳለችው አልበሽር ወደ ዓለም አቀፍ የጦር ወንጀለኞች ፍ/ቤት ይላክ አይላክ የሚለውም ክፍፍል ፈጥሯል፡ ፡ ወታደሩ ራሱ የበሽር፣ የቡርሃንና "ልዩ ኃይል" በሚል ተከፋፍሏል፡፡ ስለዚህ እኔ የሚያሰጋኝ ሱዳን ኢትዮጵያን መጥታ ታጠቃለች የሚለው ሳይኾን ሱዳን ስትፈረካከስ በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጠረውን ጫና እንዴት መቋቋም አለብን የሚለው ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በድንበር በኩል ያለው ጉዳይ ሲኾን እነ ቡርሃን ሰሞኑን "ኢትዮጵያ አጠቃችን" ብለው አንድነት ለመፍጠር እየሞከሩ ነው፡ ፡ ግን ችግራቸው ከዚያ ስለባሰ ሊሠራላቸው አልቻለም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም ያደረገው ነገር የለም፡፡ ጉዳዩንም በስምምነት እንፈታዋለን ብሏል፡፡ አልቡርሃንም ቱርክ ሄዶ የተናገረው በዲፕሎማሲ እንደሚፈታ ነው፡፡ በኬንያ በኩል ያለው ጉዳይ ለእኔ የሚታየኝ ሀገሪቱ በድኅማ እንደምትኖር ነው፡፡ እንደሚታወቀው አሁንም የእንግሊዝ ቅኝ ናት፡፡ የሰው አዕምሮ በቅኝ አገዛዝ ሥር ነው፡፡ ነጭ ያመልካሉ፤ ድኅማውም አለ፡

፡ የብሔር፣ የጎሳ ጉዳዩም ተዳፍኖ የተቀመጠ ነገር ነው፡፡ በኩኩይና በኢሱ ጎሳ አባላት መካከል ትልቅ ችግር አለ፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ የህወሓት ዐይነት የጎሳ ቡድን እንዲህ ዐይነት ወንጀል ፈጽሞ አገር ገነጣጥሎ ሥልጣን ላይ ከመጣ ለሌሎችም ምሳሌ እንደሚኾን ነው፡፡ በኬንያም ይሁን በሌላ ቦታ የዚህ ቡድን ምሳሌነት ጎልቶ ይወጣል፡፡ በመኾኑም ከኢትዮጵያ እኩል አደገኝነቱን መጠንቀቅ ነው ያለባቸው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም ከወያኔዎች ጋር ድርድር ቢጀምር፣ ሌሎቹም በዚያ መንገድ መደራደር ይኖርባቸዋል፡፡ ይኽ ደግሞ አዋጪ ስላልሆነ ለአፍሪካ ሰላም ሲባል የግዴታ ወያኔ መጥፋት አለበት፡፡ አለዚያ ማንኛውም የጎሳ ቡድን እየተነሳ መንግሥት ገልብጬ እገዛለሁ የሚል ነገር ይመጣል፡፡ በአጠቃላይ ኬኒያ የራሷ ችግር አለባት፡፡ ችግሯን የምትፈታውም አሸከር በመኾን ነው፡፡ ኢትዮጵያን ግን ደፍረው ይነኳታል ብዬ አላምንም፡፡ በተመድም ከኢትዮጵያ ጎን መኾናቸውን አረጋግጠዋል፡

ሌላው ጉዳይ ግብፅ ናት፡፡ የግብፅ ችግር አፍጋኒስታን ናት፡፡ ምክንያቱም ታሊባኖች ያን ሁሉ ጦርነት አድርገው አሜሪካን ካባረሩ በኋላ ሁሉም አሸባሪዎችን ንቃት እንዲኖራቸውና “አስር ዓመትም ታግለን እናሸንፋለን” ወደሚል ሞራል እንዲሸጋገሩ ስንቅ ሆኖላቸዋል፡፡ ይሄ በግብፅ ለሚገኙት የሙስሊም ወንድማማቾች አቀንቃኞች ይጠቅማል፡፡ ሙስሊም ወንድማማቾች ከመቶ ዓመት በላይ የቆዩ ነው፡፡ ሶሪያም ነበሩ፤ ሌላም ቦታ አሉ፡፡ የግብፅ መንግሥትም ሥጋት ይኼው ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያን አይሞክራትም ብዬ ነው የማስበው፡፡ ምክንያቱም ለራሱ ስለሚያሰጋውም ጭምር ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት አይከፍትም፡፡ ሱዳንና ግብፅም የራሳቸው የድንበር ችግር አለባቸው፡፡ ለጊዜው ግን ሸፋፍነውታል፡፡ ስለዚህ የእነርሱ ጦር ኢትዮጵያ መጥቶ የሚያመጣው አንዳች ነገር አይኖርም፡፡ ጦርነት እንክፈት እንኳን ቢሉ የግድቡን ውሃ አንድ ቀን ብንለቀው ሁሉንም ጠራርጓቸው ይኼዳል፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ለማጥቃት የሚመጡ ኃይሎች ሁሉ እየወደሙ ነው የሚመለሱት፡፡ አሜሪካም ብትሆን ኢትዮጵያን ከነካች ትጠፋለች፡፡ አሁን እያየን የመጣነውም እሱን ነው ፤ ሀገሪቱ በመጥፋት ላይ ነው ያለችው፡፡

**ግዮን፡- አሜሪካ አሁን ላይ ከአውሮፓውያን ጋር ያላት ቁርኝትስ እንዴት ይቃኛል?**

ፐ/ር አለማየሁ፡- በፈረንሳይ ምሳሌነት እንየው፤ ፈረንሳይ ከአውስትራሊያ ጋር የባህር ሰርጓጅ መሣሪያ ለመሥራት ስምምነት ነበራት፡፡ አሜሪካኖች በጎን ሄደው እነደጩልሌ የፈረንሳይን ውል መነተፉ፡፡ በዚህም በፈረንሳይና በአሜሪካ መካከል ትልቅ ቅራኔ ተፈጥሯል፡፡ የፈረንሳዩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሜሪካኑን ሙልጭ አድርጎ ነው የተሳደበው፡፡ እንዲዚህ ተዋርደው ሲወጡ እኛንም አዋረዱን ነው ያለው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ባይደን “አሜሪካ ትመልሳለች” እያለ አጋር የሚባሉትን ሀገራት መሬት ላይ ጥሏቸው ነው የሄደው፡፡ ታማኝነት እና ክብር የለም፡፡ ስለዚህ አሜሪካ እየወደቀች የምትሄድ ሀገር በመኾኗ ዓለምም እየተቀየረ ነው፡፡ “ልዕለ ኃያል”(ሱፐር ፓወር) የሚለው ነገር ቀርቶ “መልቲ ፓወር” እና “ሪጅናል ፓወር” እየኾነ መጥቷል፡፡ የአሜሪካ እየወደቀች መምጣት ብዙዎችን እያመኑበት የመጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ተንቃለች፡፡ የተናቀ ሀገር ደግሞ የሚያመጣው ነገር የለም፡፡ አሜሪካ በዘመኗ ያሸነፈችው ጦርነት የለም፡፡ ሕዝቡም በየሀገሩ እየሄደ መሞት ሰልችቶታል፡፡ ባይደን በሥልጣን አይቆይም፡፡ አራት ዓመቱን ከጨረሰ እድሜውም አይፈቅድለትም፡፡ ከዚያ በኋላ የሚመጣው ደግሞ የትራንፕ ዐይነት ነው፡፡ ዓለምም የሚጠብቀው ይኼን ነው፡፡ አውሮፓውያንም ይኼን ነቅተውበታል፡፡ አሜሪካ ታማኝ ልትሆን ስለማትችል በራሳችን እንቁም እያሉ ነው፡፡



**ግዮን፡- “ነጩ ፖስታ ለነጩ ቤተመንግሥት” የተሰኘው የፊርማ ማሳበሰብ ሥራ ምን ያህል ለውጥ ይመጣል ብለው ያስባሉ?**

ፐ/ር አለማየሁ፡- አንደኛ እውነት ለመናገር የአሜሪካ መሪዎች ለዚህ ቁብም አይሰጡት፡፡ ሕዝብ ስለጮኸ ምንም አያደርጉም፡፡ በዚያ ላይ ይሄ ኦንላይን የማይታወቅ ነገር ነው፡፡ ለዚህ ደንታ የላቸውም፡፡ ከአሁን በፊትም ተሞክሮ አንዲት ውጤ አላመጣም፡፡ ነገር ግን ሕብረተሰቡን ለማሳተፍ ይህ ዓይነቱ እንቅስቀሴ ጥሩ ነው፡፡ አብዛኛው ኮሜንት ማን እንደ ፃፈው አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ሰሞኑን ዳያስፖራው አንድ የሚያደርገው የሜሴጂ ዘመቻ አለ፡፡ በዚህ ሜሴጅ ዲያስፓራው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መኾኑን ይገልፃል፡፡ ይኼ ማለት ደግሞ ለእነርሱ ትልቅ ውርደት ነው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የሚያስቡት እነዚህን ሰዎች ይዘው ሃሳባችን ማሳካት ነበር፡፡

**ግዮን፡- ስለአዲሱ የመንግሥት ምሥረታ ምን መልዕክት ማስተላለፍ ይፈልጋሉ?**

ፐ/ር አለማየሁ፡- ማስተላለፍ የምፈልገው አድናቆቴን ነው፡፡ አድናቆቴ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አንደኛ የዓለም በተለይ የምዕራቡ ዓለም ኢትዮጵያውያን ለዴሞክራሲ አልተዘጋጁም ይሉን ነበር፡፡ ሁለተኛ ቢዘጋጁም በዘር ስለተከፋፈሉ ምርጫ ማድረግ አይችሉም ብለውን ነበር፡፡ ምርጫ ሀገሪቱን ይከፋፍላል ብለው ፕሮፓጋንዳም ሰርተው ነበር፡፡ ያን ሁሉ ኩም አድርገን በሥነ ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ ለመንግሥት አክብሮቴን መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በአሁኑ ጊዜ ሁላችንም አንድነታችንን መጠበቅ አለብን፡፡ ምክንያቱም የውስጥም የውጭም ጠላቶች ስላሉን በመሃላችን ክፍተት ካገኙ በዚያ ክፍተት ላይ ኾነው የለመዱትን ሴራ አሲረው ለማጥፋት ይሞክራሉ፡፡ ያን ክፍተት መዝጋትና ጽናት ባለው መንገድ መሥራት አለብን፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ ይህን ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡ ጠላቱን አውቆ ተዘጋጅቶ መጠበቅ አለበት፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የማስተላልፈው መልዕክት አሁን ሕዝብ የመረጠው መንግሥት ስላለ ያንን መንግሥት መደገፍ እንደሚያስፈልግ ነው፡፡ የመረጠው ሕዝብ መደገፍ አለበት፡፡ ሲያጠፋ እንዲቀጣ ጥሩ የሠራም እንዲመሰገን ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ይህ ለውጭም ለውስጥም ጠላቶች የሚልከው መልዕክት አለ፡፡ ዴሞክራሲም በዚህ መልኩ ነው እየዳበረ የሚሄድው፡፡ ዴሞክራሲ ማለት የተመረጠው መንግሥት ለሕዝብ ተጠሪነትና ተጠያቂነት አለው ማለት ነው፡፡ ከተጠያቂነት ማምለጥ አይችልም፡፡ ሕዝብም ይኼን አድርጉ ማለት ብቻ ሳይኾን ተጠያቂውን አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ መንግሥትም ሕዝብን ማክበር አለበት፡፡

በመጨረሻ ኢትዮጵያዊነት በጣም ልዩ የኾነ ማንነት ነው፡፡ ስለዚህ ማንነታችንን ማወቅ አለብን፡፡ ዓለም ላይ ካለው ሰው የሚለየን ታሪካችን በቅኝ አለመገዛታችን ነው፡፡ በሃይኖታችን ልዩ ነን፡፡ የሊግ ኦፍ ኔሽን መሥራች ነን፡፡ በሀገር መሪ ደረጃ ሊግ ኦፍኔ ሽን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገሩት የኢትዮጵያው መሪ አጼ ኃይለሥላሴ ናቸው፡፡ የአፍሪካ አንድነት መሥራች ነን፡፡ የራሳችን ቋንቋ፣ የቀን አቆጣጠር ወዘተ አለን፡፡ ስለዚህ የሰለጠንን ሕዝብ ነን፡፡ ራስን ካለማወቅ ነው ብዙ ነገር የሚፈጠረው፡፡ ስለዚህ ራሳችንን እንወቅ፡፡ እኛ በሀገር ደረጃ አይደለም መታየት ያለብን፡፡ በሥልጣኔ ደረጃ ነው መታየት ያለብን፡፡ “ምዕራባዊ ሥልጣኔ” እንደሚባለው “ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔ” ተብለን መጠራት አለብን፡፡ ምክንያቱም ለሌላውም ዓለም ሥልጣኔ አጋርተናልና፡፡ ይህን ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ ይገባናል፡፡ ኢትዮጵያ ከአሁን በኋላ ወደላይ እየወጣች እንጂ እየወረደች አትሄድም፡፡ ምን ጠላት ቢመጣ ኢትዮጵያ ከአሁን በኋላ እያደገች መሄዷ የተረጋገጠ ነው፡፡

ኢትዮ ሐበሻ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ.የተ.የግ.ማህበር

# ግዮን መፅሔት ለ2013

**በአዲስ አደረጃጀትና አቀራረብ**

- **በWebsite:** http://ghion-mag.com
- **በYouTube:** Ghion-Mag Tube ግዮን መጽሔት
- **በTwiter:** Ghion Magazine
- **በTelegram:** Ghion Magazine
- **በFacebook:** Ghion-Mag ግዮን መጽሔት
- **በInstagram:** Ghion Meg

**ለአንባቢያን**

እንደምርጫው ለመድረስ በዝግጅት ላይ ነን ድርጅታችሁን በማስተዋወቅ ለአገራችን እውነተኛ መረጃ ለመስጠት የምናደርገው ጥረት እንድትደግፉና እንድታበረታቱን እንጋብዛለን፡፡

## መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን !



**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡ enqu2013@ gmail.com
ghion2011meg@gmail.com